በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም መካከል ያለው ሁኔታ እንዲሁ ነው። ዮሐ.10÷30

## 2.2.6 የመውጣት ሁኔታ

የግብርን ሶስትነት ስንመለከት ፀዓተ መንፈስ ቅዱስንና ልደተ ወልድን አንስተናል። በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ይህን ሁኔታ አብራርተን እንገነዘባለን። መጽሐፍ ቅዱስ የአብን ወላዲነትና አሥራፂነት፣ የወልድን ተወላድነት የመንፈስ ቅዱስን ሠራፂነት/ ወጭነት/ ፀዓት ወይም መውጣት በማለት አመሳስሎ ገልፆታል። ለምሳሌ ስለ አብ ወላዲነትና ስለ ወልድ ተወላዲነት ሲናገር "ከአብ ወጣሁ ወደ አለምም መጣሁ" ዮሐ.16÷18 ሲል ስለመንፈስ ቅዱስ ሠራፂነትና ስለ አብ አስራፂነት ደግሞ "ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ" ዮሐ.15÷26 በሚል በተመሳሳይ ቃል ተገልፆ ይገኛል። አባቶቻችን ሊቃውንት የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ከአብ መውጣት አሻሚነቱን አጥበው ልዩነቱን በሚያሳውቅ ልዩ ልዩ ቃል አስቀምጠውታል። ይኸውም የወልድን ከአብ መውጣት "ልደተ ወልድ" የመንፈስ ቅዱስን ከአብ መውጣት ደግሞ "ሥርፀተ መንፈስ ቅዱስ" በሚል ገልጸውታል። ልደትና ሥርፀት በሚሉት ሁለት ቃላት መሰየም ያስፈለገው በሁለቱ መካከል ሰፊ የምሥጢር ልዩነት ያለ በመሆኑ ነው። የአወጣጣቸውም አንድነትና ልዩነት እንደሚከተለው ሰፍሮአል።

አንድነቱ፡- ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁለቱም ከአብ በመውጣታቸው በአንድ ቃል ጸዓት/መውጣት/ በሚል መገለጹ ነው።

ልዩነቱ፡- ደግሞ የአወጣጣቸው ሁኔታ ነው። ወልድ ከአብ የወጣው በተወላዲነት /በልጅነት/ ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ደግሞ

በሠራፂነት /በእስትንፋስነት/ በመሆኑ ነው። ወልድ ተወላዲ እንጂ ሠራፂ አይባልም። መንፈስ ቅዱስም ሠራፂ ቢባል እንጂ ተወላዲ አይባልም። የሁለቱ ከአብ መውጣት አንድነትና ልዩነት ይህ ነው።